# ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ማስገባት ስለሚፈቀድበት ሁኔታ የወጣ የማሻሻያ መመሪያ ቁጥር 275/2013

Amending the Conditions for Allowing the Importation of Vehicles Free of Customs Duties and Taxes (Directive No. 275/2013)

የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
Ministry of Mines and Petroleum

መጋቢት 1፥ 2011

## ለማዕድን ፕሮጀክቶች ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎችን ዓይነትና ብዛት ለመወሰን የወጣውን መመሪያ ለማሻሻል የወጣ መመሪያ

ለማዕድን ፕሮጀክቶች ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎችን ዓይነትና ብዛት ለመወሰን የካቲት 1 ቀን 1999 ዓ.ም፣ የካቲት 19 ቀን 1999 ዓ.ም. እና መስከረም 28 ቀን 2000 ዓ.ም. የወጡትን እንደቅደም ተከተላቸው መመሪያ ቁጥር 1/1999 ዓ.ም.፣ መመሪያ ቁጥር 2/1999፣ መመሪያ ቁጥር 3/1999 ማሻሻልና በአንድ መመሪያ ማጠቃለል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር በማዕድን አዋጅ ቁጥር 52/1985 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ (3) አዋጁን ለማስፈፀም የሚያስችል መመሪያ ለማውጣት እንደሚችል በተሠጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### ክፍል I ጠቅላላ
### አንቀጽ 1

### አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ «ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ለማስገባት ስለሚፈቀድበት ሁኔታ በማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር የወጣ የማሻሻያ መመሪያ ቁጥር 275/2013 ዓ.ም.» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### አንቀጽ 2

### ትርጓሜ

በማዕድን አዋጅ ቁጥር 52/1985 አንቀጽ 2 እና በማዕድን ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 182/1986 አንቀጽ 2 ሥር የተተረጐሙት ቃላት በዚህ መመሪያ ውስጥ ተፈፃሚ ይሆናሉ:: ከዚህም በተጨማሪ፣

1. "ባለፈቃድ" ማለት በአዋጁ መሠረት አግባብ ካለው ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን የተሰጠ ማዕድናትን ለመመርመር ወይም ለማምረት የሚያስችል ፈቃድ ያለው ሰው ነው::

2. "አዋጅ" ማለት የማዕድን አዋጅ ቁጥር 52/1985 (እንደተሻሻለው) ነው:::

3. "ተሽከርካሪ" ማለት የደረቅና ፈሳሽ የጭነት መኪናዎችን፣ ፒክ አፕ ፎርዊል ድራይቭን፣ ስቴሽን ዋገንን፣ የሠራተኛ ማጓጓገና አውቶብስን፣ በሞተርና ያለሞተር የሚሠራ ብስክሌትን ብቻ የሚያካትት ነው::

4. "የማዕድን ውሃ" ማለት ለጤንነት ተስማሚነት ያላቸውን ማዕድናት ያየዘ ውሃ እንዲሁም ማዕድናት ከውስጡ ኢኮኖሚያዊ በሆነ ደረጃ ተለይተው ሊወጡ የሚችሉበት እንደ ብራይን ያለ ውሃ ነው:::

5. "የሚታል ማዕድናት" ማለት እንደብረት፣ እርሳስ፣ መዳብና ኒኬል የመሳሰሉ ማዕድናት ናቸው::

መዝገብ ቤት RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Mines and Petroleum

6. "የከበሩ ብረታ ብረት ማዕድናት" ማለት እንደፕላቲነም፣ ወርቅና ብር ያሉ ማዕድናት ናቸው::

7. "የኮንስትራክሽን ማዕድናት" ማለት እንደ አሸዋ፣ ጠጠር፣ ፑሚስ፣ ድንጋይ፣ የሸክላ አፈር፣ እብነበረድና ግራናይት የመሳሰሉ ማዕድናትን ያጠቃላል::

8. "የኢንዱስትሪ ማዕድናት" ማለት እንደ ካኦሊን፣ ቤንቶናይት፣ ዶሎማይት፣ ዲያቶማይት፣ ኳርትዝ እና የድንጋይ ከሰል የመሳሰሉ ማዕድናት ናቸው::

9. "የከበሩ ድንጋዮች ማዕድናት" ማለት እንደ አልማዝ፣ ሩቢ፣ ኢመራልድና ሳፋየር የመሳሰሉ የከበሩ ድንጋዮች ናቸው::

10. "የጂኦተርማል ክምችት" ማለት ለመታጠቢያ፣ ለመዝናኛ፣ ለሕክምናና ለኃይል ማመንጨት አገልግሎት የሚውል የጂኦተርማል እንፋሎት ነው::

11. "ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን" ማለት እንደአግባቡ የብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር የማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ወይም የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር ነው::

12. "ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸው ማዕድናት" ማለት ለዚህ መመሪያ ጠቀሜታ ብቻ የከበሩ፣ የኢንዱስትሪና የድንጋይ ከሰል ማዕድናት ናቸው::

## አንቀጽ 3
## የተፈጻሚነት ወሰን

1. ይህ መመሪያ በማዕድን ዘርፍ በተሰማሩ ባለፈቃዶች ላይ ተሽከርካሪዎችን በሚመለከቱ ጉዳዮች ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል::

2. መመሪያው በነዳጅና በኢነርጂ ሥራዎች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም::

3. ለማዕድን ፕሮጀክቶች ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎችን ዓይነትና ብዛት ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 1/1999፣ መመሪያ ቁጥር 2/1999 እና መመሪያ ቁጥር 3/1999 በዚህ ማሻሻያ መመሪያ የተተኩ ስለሆነ ተፈጻሚ አይሆኑም::

## ክፍል ሁለት
## ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥና ታክስ ነጻ ለማስገባት የሚፈቀድላቸው የፈቃድ ዓይነቶችና የአፈቃቀድ ሁኔታ

## አንቀጽ 4
## ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ ለማስገባት የሚችሉ ባለፈቃዶች

1. ማንኛውም የምርመራ፣ የአነስተኛ ደረጃ፣ የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ወይም ምርመራና ማምረትን ያጣመረ ፈቃድ ያለው ሰው ወይም አግባብ ባለው ሕግ



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

መሠረት የተደራጀ የማዕድን የሕብረት ሥራ ማህበር በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሠረት ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ ማስገባት ይፈቀድለታል፡፡

2. ማንኛውም የምርመራና ማምረትን ያጣመረ ፈቃድ ያለው ሰው በምርመራና በማምረት ሥራ የተፈቀደውን ተሽከርካሪ የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት ያገኛል፡፡

3. ማንኛውም የፍለጋ ፈቃድ ወይም የባህላዊ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ያለው ሰው ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ ማስገባት አይፈቀድለትም፡፡

## አንቀጽ 5
## ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ ማስገባት ስለሚፈቀድበት ሁኔታ

ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ የሚገቡ ተሽከርካሪዎች ዓይነትና ብዛት በማዕድን ፈቃድ ዓይነት፣ በማዕድን ዓይነትና በፕሮጀክቱ አጠቃላይ የኢንቨስትመንት መጠን የተለያዩ እርከኖች ላይ ተመሥርቶ የሚወሰን ሆኖ ዝርዝር አፈጻጸሙ ከዚህ መመሪያ ጋር የመመሪያው አካል ሆኖ በተያያዘው ሠንጠረዥ 1፣ 2 እና 3 በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 6
## አስፈላጊ ማስረጃዎችን ስለማቅረብ

በዚህ መመሪያ መሠረት ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ ለማስገባት የሚጠይቅ ማንኛውም ባለፈቃድ በቅድሚያ የሚከተሉትን ደጋፊ ማስረጃዎች አግባብ ላለው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ መብት አስፈፃሚ አካል ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

1. አግባብ ካለው ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን የተሰጠውን የማዕድን ሥራ ፈቃድ (ከዋናው ጋር የተገናዘበ) ፎቶ ኮፒ፣ የሕብረት ሥራ ማህበር ከሆነ በአግባቡ የተመዘገበ ስለመሆኑ አግባብ ካለው ባለሥልጣን የተሰጠውን የምስክር ወረቀትና የማዕድን ሥራ ፈቃድ ማስረጃ፣

2. የፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ስለመጀመሩ ማለትም የካምፕ ዝግጅት፣ መሠረተ ልማትና የመሳሰሉት ሥራዎች እየተሠሩ ስለመሆናቸው ከፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የተሰጠ ማስረጃ፣

3. የማዕድን ማምረት ሥራ ሲሆን ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ከተጠቀሱት በተጨማሪ ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉ ካፒታል ዕቃዎች ከውጭ አገር ስለመግባታቸው የግዢ ደረሰኝ (Invoice) እና ቢል ኦፍ ሌዲንግ (Bill of Loading) ወይም ኤርዌይ ቢል (Air wat Bill) የካፒታል ዕቃዎቹ ከአገር ውስጥ የተገዙ ከሆነ የግዥውን ውል ማስረጃ እና፣

4. የሠራተኛ ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎች ለማስገባት የሚቀርብ ጥያቄ ሲሆን ለፕሮጀክቱ ተቀጥረው በመሥራት ላይ የሚገኙ ሠራተኞችን ስም ዝርዝር የያዘ የደመወዝ መክፈያ ሰነድ (Payroll)፣



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

## አንቀጽ 7
## በአገር ውስጥ ስለሚገጣጠሙ ተሽከርካሪዎች

ተሽከርካሪ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ እንዲያስገባ የሚፈቀድለት ባለፈቃድ ከአገር ውስጥ የተሽከርካሪ መገጣጠሚያ ፋብሪካ ተሽከርካሪ ሲገዛ አግባብ ካለው አካል በሚያቀርበው ማስረጃ መሠረት ተሽከርካሪውን ለማምረት ከውጭ ተገዝተው በገቡ የተሽከርካሪው ግብአቶች ላይ የተከፈለ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ተሰልቶ ይቀነስለታል፡፡

## ክፍል ሦስት
## ልዩ ልዩ
## አንቀጽ 8
## ስለተጨማሪ ኢንቨስትመንት

ፈቃድ ከወሰደ በኂላ ተጨማሪ ኢንቨስትመንት በመመደብ የማዕድን ሥራውን ያስፋፋ ባለፈቃድ በአዲሱ የኢንቨስትመንት እርከን የሚፈቀድለትን የተሽከርካሪ ዓይነትና ብዛት በቀድሞው የኢንቨስትመንት እርከን ከተፈቀደለት ጋር በማገናዘብ ልዩነቱን ብቻ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ለማስገባት ይችላል፡፡

በዚህ መመሪያ የተመለከተው ቢኖርም ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ እንዲያስገባ ከሚፈቀድለት የ ሽከርካሪ ዓይነትና ብዛት በላይ ለማስገባት በማይፈቀድለት የሥራ መስክ የተሰማራ ማንኛውም ባለፈቃድ ለፕሮጀክቱ አግባብነት ያላቸው ተሽከርካሪዎች ተገቢውን የጉምሩክ ቀረጥና ክስ በመክፈል ማስገባት ይችላል፡፡

## አንቀጽ 9
## መመሪያው ስለሚገድባቸውና ስለማይገድባቸው ሁኔታዎች

1. ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት በዚህ መመሪያ የተፈቀደውን የተሽከርካሪ ዓይነትና ብዛት ወይም ከዚያ በላይ ከቀረጥና ታክስ ነጻ ያስገባ ባለፈቃድ ተጨማሪ ተሽከርካሪ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ ማስገባት አይችልም፡፡

2. በዚህ መመሪያ የተመለከተው ቢኖርም ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ እንዲያስገባ ከሚፈቀድለት የተሽከርካሪ ዓይነትና ብዛት በላይ ለማስገባት የሚፈልግ ማንኛውም ባለፈቃድ እና ከቀረጥና ታክስ ነጻ እንዲያስገባ የማይፈቀድለት ባለፈቃድ ለፕሮጀክቱ አግባብነት ያላቸውን ተሽከርካሪዎች ተገቢውን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ በመክፈል ማስገባት ይችላል፡፡

3. በማንኛውም የማዕድን ሥራዎች ከ500 ሚሊዮን ብር በላይ ኢንቨስት ያደረገ ባለፈቃድ ወይም ለሀገራችን ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ባላቸው ማዕድናት ምርመራና ማምረት ሥራ የተሰማራ ባለፈቃድ በዚህ መመሪያ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲያስገባ ከሚፈቀዱለት በተጨማሪ ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ ለማስገባት ጥያቄ ሲያቀርብ ጥያቄው በማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር እየተወሰነ ለገቢዎች ሚኒስቴር በሚፃፍ ደብዳቤ መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

4. ለማዕድን ሥራ የሚፈቀደው ስቴሽን ዋገን ፎር ዊል ድራይቭ (4WD)፣ ሎንግ ዊል ቤዝ (Long wheel base)፣ በናፍታ የሚሠራ (diesel) በተለምዶ ለአምቡላንስ የሚያገለግል ቶዮታ ላንድክሩዘር ሞዴሎች ወይም ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ለመስክ ሥራ አመቺ የሆኑ ተሽከርካሪዎችን ብቻ ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማና አካባቢዋ ላሉ የኢንዱስትሪና የኮንስትራክሽን እንዲሁም የማዕድን ውሃ ማምረት ሥራ ፈቃዶች አይፈቀድም።

5. በዚህ መመሪያ «ሠንጠረዥ 3» የተፈቀደውን ስቴሽን ዋገን ተሽከርካሪ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ ለማስገባት የተቀመጠውን የፈቃድ ዓይነት፣ የማዕድን ዓይነትና የኢንቨስትመንት መጠን የሚያሟላ ማንኛውም ባለፈቃድ «በሠንጠረዥ 2» የተመለከተውን ፒክ-አፕ ተሽከርካሪ ብቻ ወይም «በሠንጠረዥ 3» የተመለከተውን ስቴሽን ዋገን ብቻ እንደ ሥራው አስፈላጊነት መርጦ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማረጋገጫ ሲያገኝ ማስገባት ይችላል።

## አንቀጽ 10
## መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከዛሬ ሰኔ ------ ቀን 2001 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሰኔ ------ ቀን 2001 ዓ.ም.
የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር
አዲስ አበባ

አለማየሁ ተገኑ
ሚኒስትር

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

ሠንጠረዥ 1

| ተ.ቁ | የፈቃድ ዓይነት | የማዕድን ዓይነት | ኢንቨስት የተደረገ የካፒታል መጠን (በብር) | የተሽከርካሪ ዓይነት | ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ምርመራ | ለሁሉም ማዕድን | 1 - 5 ሚሊዮን | • ፒክ አፕ (4WD) | 1 |
| | | | ከ5 ሚሊዮን በላይ | • ፒክ አፕ (4WD) | 2 |
| 2 | ምርት | ማዕድን ውሃ | ከ5 -15 ሚሊዮን | • ፒክ አፕ (4WD) | 1 |
| | | | | • ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 2 |
| | | | | • ሞተር ብስክሌት | 1 |
| | | | | • ብስክሌት | 5 |
| | | | ከ15.1 - 30 ሚሊዮን | • ፒክ አፕ (4WD) | 2 |
| | | | | • ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 2 |
| | | | | • ከ5-10 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ<br>ወይም<br>ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 1<br><br>2 |
| | | | | • ሞተር ብስክሌት | 2 |
| | | | | • ብስክሌት | 5 |
| | | | ከ30.1 ሚሊዮን በላይ | • ፒክ አፕ (4WD) | 2 |
| | | | | • ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 3 |
| | | | | • ከ5-10 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ<br>ወይም<br>ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 2<br><br>5 |
| | | | | • ሞተር ብስክሌት | 3 |
| | | | | • ብስክሌት | 5 |

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum
RECORD

| ተ.ቁ | የፈቃድ ዓይነት | የማዕድን ዓይነት | ኢንቨስት የተደረገ የካፒታል መጠን (በብር) | የተሽከርካሪ ዓይነት | ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ሜታልና የከበሩ ብረታ ብረት | ከ8-15 ሚሊዮን | • ፒክ አፕ (4WD) | 3 |
| | | | | • አምቡላንስ | 1 |
| | | | | • ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 1 |
| | | | | • ከ5-10 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ<br>ወይም<br>ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 1<br><br>2 |
| | | | | • የምርት ማጓጓዣ ልዩ ተሽከርካሪ (ለወርቅ፣ ለፕላቲኒየምና ለብር) | 1 |
| | | | | • ቦቴ መኪና | 1 |
| | | | | • ሞተር ብስክሌት | 2 |
| | | | | • ብስክሌት | 5 |
| | | | ከ15.1 - 30 ሚሊዮን | • ፒክ አፕ (4WD) | 4 |
| | | | | • አምቡላንስ | 1 |
| | | | | • ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 1 |
| | | | | • ከ5-10 ቶን የጭነት መኪና<br>ወይም<br>ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 2<br><br>3 |
| | | | | • የምርት ማጓጓዣ ልዩ ተሽከርካሪ (ለወርቅ፣ ምርት ለፕላቲኒየም፣ ለብርና አልማዝ) | 1 |
| | | | | • ቦቴ ተሽከርካሪ | 1 |
| | | | | • ሞተር ብስክሌት | 2 |
| | | | | • ብስክሌት | 5 |



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Mines and Petroleum — RECORD

| ተ.ቁ | የፈቃድ ዓይነት | የማዕድን ዓይነት | የካፒታል መጠን (በብር) | የተሽከርካሪ ዓይነት | ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| | ምርት | ሜታልና የከበሩ ብረታ ብረት | 30.1 ሚሊዮን በላይ | • ፒክ አፕ (4WD) | 5 |
| | | | | • አምቡላንስ | 1 |
| | | | | • ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 2 |
| | | | | • ከ5-10 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ ወይም ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 3<br>5 |
| | | | | • የምርት ማጓጓዣ ልዩ ተሽከርካሪ (ለወርቅ፣ ምርት ለፓትነትም፣ ለብርና አልማዝ) | 1 |
| | | | | • ቦቴ ተሽከርካሪ | 2 |
| | | | | • ሞተር ብስክሌት | 4 |
| | | | | • ብስክሌት | 5 |

96/.

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

| ተ.ቁ | የፈቃድ ዓይነት | የማዕድን ዓይነት | የካፒታል መጠን (በብር) | የተሽከርካሪ ዓይነት | ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| | ምርት | የኢንዱስትሪና የኮንስትራክሽን | ከ3-15 ሚሊዮን | • ፒክ አፕ (4WD) | 1 |
| | | | | • አምቡላንስ | 1 |
| | | | | • ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 2 |
| | | | | • ከ5-10 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ ወይም ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 1<br>2 |
| | | | | • ሞተር ብስክሌት | 2 |
| | | | | • ብስክሌት | 5 |
| | | | ከ15.1-30 ሚሊዮን | • ፒክ አፕ (4WD) | 2 |
| | | | | • አምቡላንስ | 1 |
| | | | | • ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 2 |
| | | | | • ከ5-10 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ ወይም • ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 2<br>3 |
| | | | | • ሞተር ብስክሌት | 2 |
| | | | | • ብስክሌት | 5 |
| | | | ከ30.1 ሚሊዮን በላይ | • ፒክ አፕ (4WD) | 3 |
| | | | | • አምቡላንስ | 1 |
| | | | | • ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 3 |
| | | | | • ከ5-10 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ ወይም • ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 2<br>3 |
| | | | | • ሞተር ብስክሌት | 4 |
| | | | | • ብስክሌት | 5 |



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Mines and Petroleum መዝገብ ቤት RECORD

| ተ.ቁ | የፈቃድ ዓይነት | የማዕድን ዓይነት | የካፒታል መጠን (በብር) | የተሽከርካሪ ዓይነት | ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| | ምርት | የከበሩ ድንጋዮች | ከ3-15 ሚሊዮን | • ፒክ አፕ (4WD) | 1 |
| | | | | • ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 1 |
| | | | | • ሞተር ብስክሌት | 1 |
| | | | | • ብስክሌት | 5 |
| | | | ከ15.1- 30 ሚሊዮን | • ፒክ አፕ (4WD) | 2 |
| | | | | • አምቡላንስ | 1 |
| | | | | • ከ5-10 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ ወይም<br>• ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 1<br>2 |
| | | | | • ሞተር ብስክሌት | 2 |
| | | | | • ብስክሌት | 5 |
| | | | ከ30.1 ሚሊዮን በላይ | • ፒክ አፕ (4WD) | 3 |
| | | | | • አምቡላንስ | 1 |
| | | | | • ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | |
| | | | | • ከ5-10 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ ወይም<br>• ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 1<br>2 |
| | | | | • ሞተር ብስክሌት | 1 |
| | | | | • ብስክሌት | 5 |

መዝገብ ቤት RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

| ተ.ቁ | የፈቃድ ዓይነት | የማዕድን ዓይነት | የካፒታል መጠን (በብር) | የተሽከርካሪ ዓይነት | ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| | ምርት | ጨው | ከ5-15 ሚሊዮን | • ፒክ አፕ (4WD) | 2 |
| | | | | • ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 1 |
| | | | | • ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 1 |
| | | | | • ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ<br>ወይም<br>• ከ5-10 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 1<br><br>2 |
| | | | | • ሞተር ብስክሌት | 1 |
| | | | | • ብስክሌት | 10 |
| | | | ከ15.1- 30 ሚሊዮን | • ፒክ አፕ (4WD) | 3 |
| | | | | • አምቡላንስ | 1 |
| | | | | • ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 2 |
| | | | | • ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ<br>ወይም<br>• ከ5-10 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 3<br><br>2 |
| | | | | • ሞተር ብስክሌት | 2 |
| | | | | • ብስክሌት | 10 |
| | | | ከ30.1 ሚሊዮን በላይ | • ፒክ አፕ (4WD) | 3 |
| | | | | • አምቡላንስ | 1 |
| | | | | • ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 2 |
| | | | | • ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ<br>ወይም<br>• ከ5-10 ቶን የሚጭን ተሽከርካሪ | 4<br><br>2 |
| | | | | • ሞተር ብስክሌት | 3 |
| | | | | • ብስክሌት | 10 |



RECORD

| ተ.ቁ | የፈቃድ ዓይነት | የማዕድን ዓይነት | የካፒታል መጠን (በብር) | የተሽከርካሪ ዓይነት | ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| | ምርት | የጂኦተርማል ክምችት | ከ5-15 ሚሊዮን | • ፒክ አፕ (4WD) | 2 |
| | | | | • አምቡላንስ | 1 |
| | | | | • ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 1 |
| | | | | • ሞተር ብስክሌት | 2 |
| | | | | • ብስክሌት | 5 |
| | | | ከ15.1- 30 ሚሊዮን | • ፒክ አፕ (4WD) | 3 |
| | | | | • አምቡላንስ | 1 |
| | | | | • ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 1 |
| | | | | • ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ ወይም<br>• ከ5-10 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 2<br>1 |
| | | | | • ሞተር ብስክሌት | 3 |
| | | | | • ብስክሌት | 5 |
| | | | ከ30.1 ሚሊዮን በላይ | • ፒክ አፕ (4WD) | 4 |
| | | | | • አምቡላንስ | 1 |
| | | | | • ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 2 |
| | | | | • ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ ወይም<br>• ከ5-10 ቶን የሚጭን ተሽከርካሪ | 2<br>1 |
| | | | | • ሞተር ብስክሌት | 3 |
| | | | | • ብስክሌት | 5 |

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Mines and Petroleum

| ተ.ቁ | የፈቃድ ዓይነት | የማዕድን ዓይነት | የካፒታል መጠን (በብር) | የተሽከርካሪ ዓይነት | ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| | ምርት (ለህብረት ሥራ ማህበራት ብቻ) | ላሁሉም ማዕድናት | ከ1-5 ሚሊዮን | • ፒክ አፕ (4WD) | 1 |
| | | | | • ሞተር ብስክሌት | 1 |
| | | | | • ብስክሌት | 3 |
| | | | ከ5 ሚሊዮን በላይ | • ፒክ አፕ (4WD) | 1 |
| | | | | • ከ3-5 ቶን የሚጭን የጭነት ተሽከርካሪ | 1 |
| | | | | • ሞተር ብስክሌት | 2 |
| | | | | • ብስክሌት | 5 |

ሠንጠረዥ 2

| ቋሚ የሠራተኛ ብዛት | የተሽከርካሪ ዓይነትና ብዛት |
|---|---|
| ከ10 -12 | 1 አነስተኛ አውቶቡስ |
| ከ13 - 50 | 2 አነስተኛ ወይም 1 መካከለኛ አውቶቡስ |
| ከ50 በላይ - 500 | ለእያንዳንዱ ተጨማሪ 50 ሠራተኛ 1 መካከለኛ አውቶቡስ ወይም 1 አነስተኛ አውቶቡስ |

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ... የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic ... Ministry of ...

ሠንጠረዥ 3

| ተ.ቁ. | የፈቃድ ዓይነት | የማዕድን ዓይነት | የካፒታል መጠን /በብር/ | የተሽከርካሪ ዓይነት | ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ምርመራ | ለሁሉም ማዕድናት | ከ5.1-10 ሚሊዮን<br>ከ10.1 ሚሊዮን በላይ | ስቴሽን ዋገን<br>" | 1<br>2 |
| 2 | ምርት | 1. ሜታልና የከበሩ ማዕድናት<br>2. የኢንዱስትሪና የኮንስትራክሽን ማዕድናት | ከ8-15 ሚሊዮን<br>ከ15.1-50 ሚሊዮን<br>ከ50.1-100 ሚሊዮን<br>ከ100.1 ሚሊዮን በላይ | "<br>"<br>"<br>" | 1<br>2<br>3<br>4 |
| | ምርት | 1. የከበሩ ድንጋዮች | ከ20-50 ሚሊዮን<br>ከ50.1 ሚሊዮን በላይ | "<br>" | 1<br>2 |
| | ምርት | 1. ጨው<br>2. የጂኦተርማል ክምችት | ከ10-50 ሚሊዮን<br>ከ50.1 ሚሊዮን በላይ | "<br>" | 1<br>2 |
| | ምርት<br>/ለሕብረት ሥራ ማህበራት ብቻ/ | ለሁሉም ማዕድናት | ከ20 ሚሊዮን በላይ | " | 1 |

* ስቴሽን ዋገን ማለት ለመስክ ሥራ ብቻ የሚያገለግል ሆኖ ፎር ዊል ድራይቭ (4WD)፣ ሎንግ ዊል ቤዝ (long wheel base) እና በናፍጣ (diesel) የሚሠራ ለአምቡላንስ የሚያገለግለው ዓይነት ለመስክ ሥራ የሚያገለግል ተሽከርካሪ ነው።



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Mines and Petroleum
መዝገብ ቤት
RECORD